# የመቻቻልና የመከባበር እሴቶቻችን ለቀጣይ ሰላማችን ያስፈልጉናል

**ኢብሳ ነመራ**

የሙስሊሞች የመፍትሔ አፈላላጊ ጊዜያዊ ኮሚቴ በሚል የተቋቋመው ቡድን፣ ሲመሰረት ያነሳው ጥያቄ ከሁለት ወር በፊት ምላሽ ማግኘቱን እናስታውሳለን፡፡ ይሁን እንጂ "ሙስሊሙ ህብረተሰብ እንዲቀርብ ሐላፊነት ሰጥቶኛል" በሚል ይዞት ከነበረው ጥያቄዎች ሌላ ጥያቄዎች በማንሳት እንዲሁም ይዞት ለተነሳው ጥያቄ የተሰጡ ምላሾችን አፈፃፀም ወዲያና ወዲህ እየጎተተ መሙለጭለጭን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል፡፡

ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ የኮሚቴውን ጫጫታ ችላ ብሎታል፡፡ ይህን ተከትሎ የኮሚቴውን አቋም ከሚያራምዱት የተወሰኑት በስተቀር የአገር ውስጥ ሚዲያዎች ከትኩረታቸው ምህዳር ውጪ አድርገውታል፡፡

ይሁን እንጂ ኮሚቴው ወደመንግስት ተቃውሞነት ሊያድግ ይችላል ያሉትን ማንኛውንም ጉዳይ፣ እሳቱ ቢቀጣጠል ጭሱ እንኳን የማይደርስበት ርቀት ላይ ሆነው የሚቆሰቁሱና የሚያራግቡ ጥቂት የሞቱት የመንግስት ስርአቶች ናፋቂዎች የሚፈነጩበት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም* (ቪኦኤ) ትውልደ ኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ጋር ፍቅሩ ደርጅቷል፡፡ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀው የግንቦት 7 ልሳን የሆነው ኢሳትም "የምትበጠብጡ ከሆነ ዝምድናችሁን አጥብቄ እሻዋለሁ ጡት እንጣባ" እያላቸው ነው፡፡

የሙስሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ የተባለው ቡድን ሲመሰረት አንስቶት የነበረውና ለመመስረቱም ቀዳሚውና ዋነኛው ምክንያት የነበረው፣ አሁን በስራ ላይ ያለውን የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት (መጅሊስ) በምርጫ እንዲተካ ማድረግ ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ ለማስፈፀም ሰሞኑን የኢትዮጵያ ኡላማዎች (ሃይማኖታዊ ምሁራንስ) ም/ቤት የምርጫ ፕሮግራም ይፋ አድርጓል።

የኡላማዎቹ ም/ቤት ባወጣው የምርጫ ሰሌዳ መሰረት፣ ነሀሴ 21፣ 25ና 28 ቀን 2004 ዓ/ም በቀበሌ፣ በወረዳና በዞን ደረጃ፣ ጳጉሜን 1 ቀን 2004 ዓ/ም በክልል እንዲሁም መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ/ም በአገር አቀፍ ደረጃ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ምርጫ ይካሄዳል።

የኡላማዎች ም/ቤት የምርጫውን ሂደት አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ በየደረጃው የሚያስፈልጉ አስመራጭ አካላትን በህዝብ ሙስሊሙ በግልፅና በቀጥታ እንደሚያስመርጥና አስመራጭ አካሉም

በቀጥታ የስራ አስፈፃሚ እንደሚያስመረጥ፣ አስመራጭ አካሉ በሁሉም ደረጃዎች ገለልተኛ ሆኖ ምርጫው ነፃ የህዝብ ውክልናን በሚያንፀባርቅ አኳኋን እንዲካሄድ የሚደረግ መሆኑን አስታውቋል።

የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ግን ይዞት ለተነሳው ጥያቄ የተሰጠውን  ምላሽ የአፈፃፀም ሂደት አልተቀበለም፡፡ “ምረጫው በቀበሌ፣ በወረዳ፣ … ደረጃ መካሄድ የለበትም” በሚል በጉዳዩ ላይ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ በይፋ ከገለፀው አቋም በተጨማሪ ሌላ መቃወሚያ አቅርቧል።

ኮሚቴው ቀደም ሲል አሁን በስራ ላይ ያለው መጅሊስ ምርጫውን ሊያካሂደው አይገባም ነበር ያለው። ሆኖም ምርጫው ገለልተኛ በሆነው የኡላማዎች ምክር ቤት አማካኝነት የሚካሄድ መሆኑ ሲገለፅ ይህንንም ተቃውሟል።

የኮሚቴው ሰብሳቢና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እንደሆኑ የሚነገረላቸው፣ የአሜሪካ ድምፅ የአማርኛ ፕሮግራም ያገነናቸውና ያስተዋወቃቸው አቡበከር አህመድ (አንዳንዴ አቶ ሌላ ግዜ ደግሞ ኡዝታዝ ይሏቸዋል) ለዛው ለደንበኛቸው ቪኦኤ በሰጡት መግለጫ “ምርጫው በኡላማዎች ም/ቤት አስተባባሪነት የሚካሄድ መሆኑን አንቀበለውም፤” ብለዋል። የኡላማዎች ም/ቤት ያወጣውን መግለጫ ተከትሎም ዓርብ ሰኔ 2 ቀን 2004 ዓ/ም በአአዲስ አበባ የተቃውሞ ሰልፍ መደረጉንም አቶ አቡበከር ተናግረዋል።

የግንቦት 7 ልሳን የሆነው ኢሳት አቶ አቡበከርን በቀጥታ ባይጠቅስም፣ እርሳቸው የሚመሩት ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ የመጅሊስ አባላትን ምርጫ ተቃውመው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸውን አውርቷል። በዚህ “ሰላማዊ ሰልፍ” ላይ “ቀበሌ የካድሬ መፈልፈያ እንጂ የሙስሊም መሪዎች መምርጫ አይደለም” የሚል መፈክር መፎከሩን ነግሮናል።

ይህን አቶ አቡበከር የሚመሩትን ኮሚቴ አካሄድ፣ የኡላማዎች ምክር ቤቱን ማንነት እንዲሁም የመጅሊሱ ምርጫ በቀበሌ፣ በወረዳ ማካሄድ ለምን እንዳስፈለገ እንመልከት።

ቀደም ሲል እንደገለፅነው አቶ አቡበከር የሚመሩት መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ የመጅሊሱን ምርጫ በተመለከተ “ከመንግስት ጋር ካልተወያየሁ ሞቼ እገኛለሁ” ብሎ በተወያየበት ወቅት፣ በሥራ ላይ ያለው መጅሊስ በሌላ ይተካ  ከማለት ውጭ ሌላ ጥያቄ እንዳላቀረበ እናስታውሳለን። መንግስት ይህ ጉዳይ እንደማይመለከተው ገልፆ፣ ሆኖም የሙስሊሙ ጥያቄ እንደህዝብ ጥያቄ ተገቢ ስለሆነ ምርጫው እንዲካሄድ በሚል መግባባት ላይ ተደረሰ።

የእነ አቡበከር ኮሚቴ በተገኘበት በተደረገው ውይይት በተደረሰበት መግባባት መሰረት ምርጫውን የማድረግ ዝግጅት ተጀመረ። ይሄኔ ኮሚቴው በጠየቀው መሰረት ምርጫው መካሄዱ ቁርጥ መሆኑን

ሲያውቅ፣ በቀበሌና በወረዳ መካሄድ የለበትም የሚለውን ወሬ አስወርቶ ቅስቀሳ ማካሄድ ጀመረ፤ ይህ ጉዳይ ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ የመነጨ ሳይሆን ኮሚቴው ፈብርኮ ቁልቁል ያወረደው ነው።

እዚህ ላይ ብዙዎቹ “ምርጫውን በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ማድረግ ለምን አስፈለገ?” የሚል ጥያቄ ሊያነሱ ይችሉ ይሆናል። ምርጫው በቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል… ደረጃ እንዲካሄድ የተደረገው አሁን ኃላፊነት ላይ ባለው መጅሊስ ውሳኔ አይደለም። ከዚህ ይልቅ በእሰልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት መተዳደሪያ ደንብ በሚያዘው መሰረት ነው። ከዚህ ቀደምም የመጅሊስ አባላት ምርጫ በዚሁ ደንብ መሰረት ነው ሲካሄድ የቆየው፡፡

የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ደንብ ሰለ ምክር ቤቱ ምርጫ የሚያዘው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምርጫው በቀበሌ ደረጃ መካሄዱ በራሱ እነአቶ አቡበከር እንደሚሉት በመስጂድ ከመካሄድ የተሻለ ትክከለኛ የህዝብ ሙስሊሙ ውክልና ያላቸውን የመጅሊስ አባላት ለመምረጥ የሚያስችል ሆኖ እናገኘዋለን።

ምረጫ የህዘብ ውክልና ነው። ሙስሊሙ በተለይ ከተለያየ አካባቢ በብዛት ወጥቶ በሚሰግድበት የዓርብ (ጁመአ) ስግደት ላይ ከሚያገኛቸው ምዕመናን ይልቅ፣ በአንድ አካባቢ አብረው የሚኖሩትን ማንነት የበለጠ ያውቃል። በመሆኑም በትክክል የሃይማኖቱ እውቀት ያላቸውን፣ የሃይማኖት ተቋማቱን የመምራት ስነምግባርና ክህሎት ያላቸውን መምረጥ የሚችለው ምርጫው በቀበሌ ደረጃ ቢካሄድ ነው።

እነአቡበከር ይህን የምረጫ አካሄድ የሚቃወሙት ምክንያት አላቸው፡፡ ይህም በአጠቃላይ ምርጫው በሰከነ መንፈስ እንዳይካሄድ ከመፈለግ የመነጨ ነው። በሰከነ መንፈስ ከተካሄደ እንደሚፈልጉት የቡድን አቋማቸውን በህዝበ ሙስሉሙ ላይ መጫን የሚያስችላቸው ክፍተት የሚያስገኛቸውን ውክልና የማግኘት ዕድላቸው ይጠባል፡፡

በዚህ ምክንያት ሁኔታው ያለወጉ ተጠምዝዞና ተዋክቦ በግርግር ከስርዓት ውጭ የሆነ ምርጫ የሚካሄድበትን ሁኔታ መፍጠር ይሻሉ። እኔ እንደሚገባኝ ኮሚቴው የመጅሊሱ መተዳደሪያ ደንብ ወደጎን ተትቶ ምርጫው በሰከነ መንገድ በመስጂድ ደረጃ ይካሄድ ቢባልም ከመቃወም አይመለስም፡፡

የኮሚቴው መድረሻ ምርጫው ተካሂዶ ሕዝበ ሙስሊሙ የሃይማኖት መሪዎቹን መሰየሙ ሳይሆን፣ ወከባ በመፍጠር ሙስሊሙንም ሙስሊም ያልሆነውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በማደናገር፣ ሁኔታውን የፖሎቲካ ዓላማ ያላቸው ሰዎች ተቀብለውት እንዲያጦዙትና ውሉ እንዲጠፋ በማድረግ የቡድን ዕምነታቸውን ሕዝቡ ላይ የሚጭኑበትን ዕድል ማግኘት ነው፡፡

የመፍትሄ አፈላላጊ ተብዬው ቡድን በመስጊድ ዙሪያ በተለይ በአዲስ አበባ  አወሊያ መስጊድ ውስጥ የተደራጀ በመሆኑ፣ አንድ ሁለትም ቢሆን ውክልና የማግኘት እድል የሚኖረው ምርጫው በመስጊድ ደረጃ ሲካሄድ ብቻ እንደሆነ ያውቃል፡፡ ኮሚቴው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የሚተዳደርበት ደንብ ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንዲሻር የፈለገው ለዚህ ነው፡፡

እነ ኢሳት ሙስሊሙ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ  አደረገ እያሉ እኛ አዲስ አበባ የምንኖረውን ጭምር የትና መቼ በሚል የሚያደናግሩን በተለይ በአወሊያ መስጊድ የተሰባሰቡ ጥቂት በኮሚቴ ተብዬ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሙስሊሞች ከጁመአ ስግደት በኋላ ሰላማዊ ሙስሊሞች ስር ተሸሽገው የሚያሰሙትን ጫጫታ ነው፡፡ ይህን ከጎናቸው ከቆመ ሰው አልፎ የማይሰማ የጥቂቶች ጫጫታ ነው እንደትልቅ ነገር አግንነው ሊያስጮሁ የሚሞክሩት፡፡ ከዚህ የዘለለ አንዳችም ተቃውሞ ሊባል የሚችል የጎላ ነገር የለም፡፡

የግንቦት 7ቱ ልሳን ኢሳት “ምርጫው በቀበሌ ይካሄዳል” የሚለውን ነገር የህዝበ ሙስሊሙን አሰፋፈር ብቻ የሚመለከት ሆኖ ሳለ፣  ቀበሌ የተሰኘው የመንግስት አስፈፃሚ ተቋም የሚያካሂደው አስመስሎ የእነአቶ አቡበከርን ውዥንብር መፍጠሪያ መላ እያራገበላቸው ነው። “ቀበሌ የካድሬ መፈልፈያ እንጂ … ” የሚለው የኢሳት ወሬ ይህን ያመለክታል፡፡

ምርጫው በቀበሌ፣ ወረዳ፣ … ይካሄዳል ማለት ግን በዚህ ደረጃ በተዋቀረው የመንግስት አስፈፃሚ ተቋም አማካኝነት ይካሄዳል ማለት አይደለም፡፡  ከዚህ ይልቅ ቀበሌ፣ ወረደ … የተሰኘውን የአስተዳደር መዋቅር ለአደረጃጀት አመቺ ስለሆነ ምርጫውን የሚያካሂደው ገለልተኛ የመጅሊስ አስመራጭ አካል ይህን አደረጃጀት ይከተላል ማለት ነው፡፡  አንድም ከመንግስት ጋር የሚያተገናኘው ነገር የለም፡፡

የእስልመና ጉዳዮች ም/ቤት አደረጃጀት ራሱ፣ በቀበሌ፣ ወረዳ ፣ ዞን ፣ ክልልና አገር አቀፍ (ኢትዮጵያ) በሚል የተዋቀረ መሆኑም ሊታወስ ይገባል። ምርጫው ኮሚቴው እንደሚለው በመስጂድ ደረጃ ቢካሄድ፣ ተመራጮቹን የመጅሊሱ ደንብ ከሚያዘው አወቃቀር ጋር ማስማማት ራሱ አስቸጋሪ ስራ መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡ እንግዲህ ኮሚቴው እዚህ ዝብርቅርቀ ውስጥ መግባት የፈለገው ለጤናማ ዓላማ ነው ማለት ከእውነት የራቀ ነው፤ አለያም አስመሳይነት ነው፡፡

ኮሚቴው ያነሳው ሌላው ተጎታች አቋም፣ “ምርጫው በኡላማዎች ም/ቤት (የእስልምና ሃይማኖት ሊቃወንት ም/ቤት) መመራት የለበትም” የሚል ነው፡፡ የኡላማዎች ም/ቤት የእስልምና ሃይማኖት ሊቃውንት የተሰበሰቡበት፣ ከእስልምና ጋር የተያያዙ ስነመለኮታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር፣ ከጠቅላይ ም/ቤቱ ጋር ምንም የአዛዥ ታዛዥነት ግንኙነት የሌላው ገለልተኛ ተቋም መሆኑ ይታወቃል።

በምርጫ የሚቋቋመው የመጪው ምክር ቤት (መጅሊስ) ምርጫ የእንአቡበከር ኮሚቴ እንደጠየቀው የስራ ዘመኑን በሚያጠናቅቀው መጅሊስ አማካኝነት የማይካሄድ ከሆነ፣ ሌላ የሙስሊሙ ሕዝብ ጉዳይ የሚመለከተው በተጨባጭ ያለው ገለልተኛ አካል የኡላማዎች ም/ቤቱ ብቻ ነው። ከዚሕ የተለየ ሁሉም የኢትዮጵያ ሙስሊም የሚስማማበት ገለልተኛ አካል በተጨባጭ የለም፡፡

የእነአቡበከር ኮሚቴ አሁን በስራ ላይ ያለውን መጅሊስ አጥብቆ ስለሚቃወም ገለልተኛ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጎልቶ የወጣ አይደለም ሊባል ቢችልም የተለያየ አስተምህሮን የሚከተሉ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ባሉበት ሁኔታ በይፋ እንደሚታወቀው የሰለፊ አስተምህሮ እጥባቂ የሆነው መፍትሄ አፈላላጊ ተብዬው ኮሚቴ ገለልተኛ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡

ይህ ቡድን የመጅሊስ አባላትን ምርጫ የማካሄድ ዕድል ቢያገኝ፣ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች መሃከል ለዘለቄታው መቻቻልና መተማመን እንደሚጠፋ፣ ምናልባትም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ሙስሊም መሃከል አይተን የማናውቀው መከፋፈል እንደሚፈጠርና እንደሚሰፋ ከወዲሁ በእርግጥኝነት መናገር ይቻላል፡፡

የኮሚቴውን አካሄድ ልብ ብሎ ያስተዋለ፣ በተጨባጭ ያሉትንና ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉትን አማራጮች በሙሉ ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆን አካሄዱ፣ ምርጫው እኔ በፈልኩት አካልና አካሄድ ሊከናወን ይገባል የሚል አቋም ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም የእኔ እምነትና አቋም ብቻ ነው ትክክለኛና ተቀባቀይነት ማግኘት ያለበት በሚል መርህ የሚመራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ የአክራሪነት መርህ ነው፡፡

ገና ከጅምሩ በእስልምና ምክር ቤት ምርጫ ላይ የታየው የኮሚቴው የአክራሪነት ዝንባሌ፣ የበላይነት አግኝቶ የሙስሊሙ መሪ የመሆን ዕድል እጁ ቢገባ፣ መቻቻልን አሽቀንጥሮ ጥሎ በሃይማኖት አክራሪነት ገጥጦ አለመውጣቱን የሚያረጋግጥ አንዳችም ምድራዊ ምክንያት የለም፡፡ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ያስተዋልነው አዛውንት የመስጊድ ኢማሞችን ማይክራፎን መቀማት፣ ስለእስልምና ምንም አታውቁም የሚል ንቀትና ማንቋሸሽ፣ አልፎ አልፎም መደብደብ፤ ከመስጊድና ከአገር ወደማባረር፣ ወደግድያ .... የመሳሰሉ ፀያፍና ሕገወጥ ድርጊቶች መሸጋገሩም አይቀሬ ነው፡፡

እናም ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ከዚህ ቀደም በሙስሊሞች መሃከልም ሆነ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር በመከባበርና በመቻቻል መኖር ያስቻላችሁን፣ አባት አያቶቻችሁ በዘውዳዊው የመንግስት ስርአት በሃይማኖታቸው ላይ ይደርስ የነበረውን ጫና ተቋቁመው ሃይማኖታቸውን እንደያዙ ክፍለ ዘመናትን ተሻግረው እዚህ ማድረስ ያስቻላቸውን እሴቶች መጠበቅና ከዘመኑ ጋር አጣጥሞ ማዳበር እንደሚገባቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የፈቀዱትን ሃይማኖት ይዘው፣ የአምልኮ ስርኣታቸውን እየፈፀሙ የምድራዊ ሕይወታቸው እስከተቆረጠበት ዕለት ድረስ፣ የመፋቀርንና የመከባበርን የፈጣሪ ፍቃደ ይፈፅሙ ዘንድ፣ እስከዛሬ ተቻችለንና ተከባብረን በሰላም መኖር ያስቻለንን ነባር እሴቶቻችንን መጠበቅና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡